22

ቃለት

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

የጉምሩክ ሥነ ስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

በያሉበት

ቁጥር / Ref. No 3.1.0/78/09
ቀን / Date 11 ነሐሴ 2009.

ጉዳዩ:- የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት (ECVS) አጠቃቀም ላይ ማብራሪያ ስለመላክ

በተለያዩ የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት የሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ያለው የዋጋ መረጃ ቋት አጠቃቀምና አተማመን አፈፃፀም በተመለከተ በተደረገው ማጣራት የወጥነት ችግር መኖሩ ለማወቅ ተችለዋል:: ስለሆነም ወጥ የሆነ አፈፃፀም ይኖር ዘንድ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 እና በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 ከተደነገገው አንፃር በሚጣጣም አግባብ በሚከተለው የዋጋ መረጃ ቅደም ተከተል፣ የCPC እና የአማካኝ ዋጋ አጠቃቀም መሠረት እንዲፈፀም እያሳሰብን ከዚህ በፊት በደብዳቤ ቁጥር 3.1.0/544/08 ቀን 22 ታሕሳስ 2008 ዓ/ም ተላልፎ የነበረው ሰርኩላር በዚህ ደብዳቤ የተተካ መሆኑን እንገልፃለን::

ሀ. የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት የቅደም ተከተል አጠቃቀም በተመለከተ

1. የግብይት ዋጋ አተማመን ዘዴ /ዲክለራሲዮን አቅራቢው ዲክሌር ካደረገው ሰነድ አንፃር በማጣራት
2. የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ አተማመን ዘዴ የ3 ወር ማነፃፀሪያ መረጃ
    1. በECVS የገቡ የማነፃፀሪያ ዋጋ
        1.1 ECVS-Automatic Analysis Module
        1.2 ECVS-Query Builder Module
        1.3 ECVS-International Price Module (IP)
    2. በECVS ያልተካተቱ የዋና መ/ቤት ወቅታዊ የዋጋ ማሻሻያዎችና ውሳኔዎች
    3. በECVS ያልተካተቱ የቅ/ጽ/ቤቶች ውሳኔዎች
3. የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አተማመን ዘዴ የ3 ወር ማነፃፀሪያ መረጃ
    1. በECVS የገቡ የማፃፀሪያ ዋጋ
        1.1 ECVS-Automatic Analysis Module
        1.2 ECVS-Query Builder Module
        1.3 ECVS-International Price Module (IP)
    2. በECVS ያልተካተቱ የዋና መ/ቤት ወቅታዊ የዋጋ ማሻሻያዎችና ውሳኔዎች
    3. በECVS ያልተካተቱ የቅ/ጽ/ቤቶች ውሳኔዎች
4. ወደ ኋላ ማስላት አተማመን ዘዴ የ3 ወር ማነፃፀሪያ መረጃ



ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን !!

ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

5. በውጪ ስሌት ላይ የተመሰረተ የዋጋ አተማመን ዘዴ የ3 ወር ማነፃፀሪያ መረጃ

6. ሚዛናዊ የዋጋ አተማመን ዘዴ ማነፃፀሪያ መረጃ

1. ሚዛናዊ የአንድ ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን
2. ሚዛናዊ የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ አወሳሰን
3. ሚዛናዊ ወደ ኋላ ማስላት አተማመን ዘዴ
4. ሚዛናዊ በውጪ ስሌት ላይ የተመረተ ዋጋ

ከላይ የተቀመጠው የዋጋ መረጃ የቅደም ተከተል አጠቃቀም እንደተጠበቀ ሆኖ የECVS-Query Builder Module የዋጋ መረጃ ምንጩ በምናጣራበት ግዜ የበፊቱ ዋጋ መረጃ ለብዙ ግዜ እየተንከባለለ የመጣ ከሆነ ከECVS-International Price Module (IP) ዋጋ መረጃ በማነፃፀር የቅርብ ግዜ የሆነ ዋጋ መረጃ መወሰን ይቻላል፡፡

ለ. የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት የCPC አጠቃቀም በተመለከተ

በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት (ECVS) ለተለያየ ዓላማ የሚውሉ ዕቃዎች በተለያየ CPC ተመዝግበው የሚገቡ በመሆኑ የንግድ ሸቀጦች አማካኝ ዋጋ በሚተመንበት ግዜ በሁሉም CPCዎች በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት (ECVS) ውስጥ የገቡ የእቃዎች ዋጋ መረጃ መካተቱ እና አለመካተቱ በመመሪያው በግልፅ ያልተቀመጠ በመሆኑ ችግር እየፈጠረ መሆኑ በተደረገው ክትትል እና ስፐርቪዥን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም የንግድ ሸቀጦች አማካኝ ዋጋ በሚተመንበት እና በሚሰራበት ግዜ

1. በተለያየ CPC ለንግድ አላማ ወደ ሲስተም ከገቡ የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ እና
2. በልዩ መስተንግዶ ተስተናግደው ለንግድ አላማ ከሚውሉ (ለምሣሌ AEO) የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች ዋጋ በመውሰድ ማነፃፀር ተገቢ ይሆናል፡፡

ሐ.የጉምሩክ ዋጋ መረጃ ቋት የአማካይ ዋጋ (Weighted Average) አሰራር በተመለከተ

በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 የአንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ዕቃ አማካይ ዋጋ እንዴት እንደሚወሰድ ግልፅ ባለመሆኑ ምክንያት በአብዛኛው ቅ/ፅ/ቤቶች የዋጋ አተማመን ስርዓቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ እንደሚገኝ በተደረገው የክትትልና ድጋፍ ሱፐርቪዥን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህን ችግር ከመቅረፍ አንፃር እና ወጥ የሆነ አሰራር ከማስፈን አኳያ የአማካይ ዋጋ አሰራር ማሳያ እንደሚከተለው ተብራርተዋል፡፡

Weighted Average እና Simple Average የተለያዩ የአማካኝ ውጤት የሚያመጡ ስታስቲካዊ ቀመሮች ሲሆኑ የሚለያዩባቸው ዋና ምክንያት Weighted Average ድግግሞሽና ብዛትን መሰረት በማድረግ የሚሰራ የአመካኝ ውጤት በመሆኑ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት የአንድ ዓይነት ወይም የተመሳሳይ ዕቃዎች አማካይ ዋጋ ድግግሞሽና ብዛትን ከግምት ማስገባት ትክክለኛ የአማካይ ዋጋ አወሳሰድ የሚገልፅ መሆኑን በECVS ሞጁል Weighted Average ተቀምጧል፡፡ ይህም እንዴት እንደሚሰራ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ለማሳያ ቀርበዋል፡፡

ምሳሌ

አንድ እቃ የኤፍ ኦ ቢ ዋጋው ለመወሰን ብንፈልግ እና በECVS-Query Builder Module የአንድ ዓይነት ዕቃ ዋጋ በሶስት ወር ውስጥ 5 የተለያዩ የዋጋ መረጃ ዝርዝር እንደሚከተለው አግኝተን እንደሆነ አሁን የመጣው እቃ ኤፍ ኦ ቢ ዋጋ ስንት ይሆናል?

| የዕቃው መግለጫ | የዕቃው ብዛት(A) በቁጥር | የዕቃው ነጠላ ኤፍ ኦ ቢ ዋጋ (B) በUSD | ጠቅላላ የእቃዎቹ ድምር ኤፍ ኦ ቢ ዋጋ (C) በUSD<br>C=A*B | የወይትድ አቨሬጅ አማካይ ዋጋ አወሳሰድ አሠራር (Weighted Average Price Calculation) በUSD |
|---|---|---|---|---|
| | 2 | 10 | 20 | የአንድ ዓይነት ዕቃ አማካኝ ዋጋ=ጠቅላላ የእቃዎቹ ድምር ዋጋ (C) ሲካፈል ለጠቅላላ እቃዎች ብዛት(A) |
| | 4 | 9 | 36 | |
| XXX | 6 | 8 | 48 | = 270/34 |
| | 10 | 8.2 | 82 | |
| | 12 | 7 | 84 | = 7.94 USD |
| ድምር | 34 | 42.2 | 270 | |

አሁን ለመጣው ዕቃ ከላይ በሰንጠረዥ መሰረት ተሰልቶ የተገኘውን ዋጋ 7.94/Unit USD ኤፍ ኦ ቢ ዋጋ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ:-

- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ፅ/ቤት
- ለዋጋ መረጃ ዝግጅት አጠቃቀም ጥናት ቡድን
- ለዋጋ ትመና አ/ፕ/ል ቡድን

የኢትዮጵያገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን